King County

OFFICE OF EQUITY & SOCIAL JUSTICE

# የCOVID-19 የማህበረሰብ ድጋፍ ምንጭ መመሪያ

## Amharic COVID-19 Resource Guide

LAST UPDATED 4/22/2020

የአነስተኛ
የንግድ ድርጅት
ባለቤቶች

የኢሚግራንት
እና
የስደተኛ
ማህበረሰቦች

ስራ አጥነት
የማሕበረሰብ ጤና
የቤት አገልግሎት
ጥሬ ገንዘብ እና መሰረታዊ
አገልግሎቶች

# የ COVID-19 የመረጃ መመሪያ

ስለ ነገሮች እርግጠኛ መሆን በማይቻልበት በዚህ ወቅት፣ ቤተሰቦችዎን ለመንከባከብ የሚያስፈልግዎትን ድጋፍ ለማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። እንደ ዕድል ሆኖ፣ በርካታ መንግስታዊ ፕሮግራሞች በኮሮና ቫይረስ አለም አቀፍ ወረርሽኝ ምክንያት የብቁነት መስፈርቶቻቸውን አስፍተዋል። እርስዎ ብቁ ሊሆኑባቸው የሚችሉ የግዛት ፕሮግራሞችን ሙሉ ዝርዝር ለማግኘት፣ ይህን የዳሰሳ ጥናት ይሙሉ፡- Washington Connection። የተወሰነ አገልግሎት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ከዚህ በታች ካሉት ክፍሎች መካከል የትኛውንም መርጠው ወደሚፈልጉት የመረጃ ግብዓት ይመራሉ።

**የ COVID-19 የመረጃ መመሪያ .......... 2**
**የግንኙነት አካል፡-.......... 2**
**ስራ አጥነት.......... 3**
**የቤት አገልግሎት.......... 4**
**መሰረታዊ አገልግሎቶች .......... 6**
**የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ.......... 7**
**የምግብ ድጋፍ .......... 8**
**የሕጻናት መዋያ.......... 9**
**የ SEATTLE ከተማ ወሳኝ ሰራተኞች አጣዳፊ የልጆች እንክብካቤ ቅጽን እዚህ ማግኘት ይቻላል። .......... 9**
**ለሰነድ አልባ ፍልሰተኞች የሚያገለግሉ የመረጃ ምንጮች .......... 10**
**ለሰነድ አልባ ፍልሰተኞች የሚያገለግሉ የመረጃ ምንጮች የቀጠለ .......... 11**
**የአነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ብድር እና የአደጋ ጊዜ ድጋፍ .......... 12**
**KING COUNTY በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የመረጃ ምንጮች.......... 13**

## የግንኙነት አካል፡-

| ኢሚግራንትና ስደተኛን የሚመለከቱ ጥያቄዎች | የቋንቋ ተደራሽነትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች |
|---|---|
| **Hamdi Mohamed**<br>Immigrant and Refugee Policy Advisor<br>Hamdi.mohamed@kingcounty.gov | **Senayet Negusse, M.Ed. (sun-night)**<br>Language Equity Program Manager<br>Office of Equity & Social Justice<br>**snegusse@kingcounty.gov** |

# ስራ አጥነት

በኮሮና ቫይረስ አለም አቀፍ ወረርሽኝ ምክንያት ስራዎትን ካጡ፣ ለስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ለማመልከት ፈጣኑ መንገድ በ WA Employment Security Department (የስራ ቅጥር የደህንነት ክፍል) ድረ ገጽ በኩል ነው። በ COVID-19 ምክንያት ከስራዎት ከተቀነሱ፣ የግልዎ ተቀጣሪ ቢሆኑም ወይም የሚፈለገውን መደበኛ 680 ሰዓት ባይሰሩም እንኳን ብቁ የመሆን ዕድል አለዎት። የ Lyft እና Uber ሰራተኞችም በዚህ ውስጥ ይካተታሉ። በተጨማሪም፣ የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት የሚያስፈልገው የአንድ ሳምንት የጥበቃ ጊዜም እየቀረ ነው። በተጨማሪም፣ የፌዴራል የኮሮና ቫይረስ ማነቃቂያ ፓኬጅ እስከ ጁላይ 31 ድረስ በእያንዳንዱ ሳምንታዊ የስራ አጥነት ክፍያ ላይ የ $600 ጭማሪ አድርጓል።

ከማመልከትዎ በፊት፣ ይህን መረጃ ማዘጋጀትዎን እርግጠኛ ይሁኑ (ESDWA)፡

- **የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥሮችዎ።** ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ይህን መረጃ እንዲሰጡ የፌዴራል ሕግ ይጠይቅዎታል።
- **ለመጨረሻ ጊዜ የሰሩበት ቀጣሪ ስምና አድራሻ፣** የሰሩበት ጊዜ ምንም ያህል ቢሆን ወይም የሰሩት ስራ የትኛውም ዓይነት ቢሆንም ጭምር።
- ለመጨረሻ አሰሪዎ **ለመጨረሻ ጊዜ የሰሩበት ቀን**። ሲስተሙ ማናቸውንም የወደፊት ቀናት አይቀበልም። እስካሁን እየሰሩ ከሆነ፣ ያመለከቱበትን ቀን መጠቀም ይችላሉ።
- **ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የሰሩባቸው ቀጣሪዎች በሙሉ ስምና አድራሻ።** ባለፉት ሁለት ዓመታት የሰሩባቸውን ቀጣሪዎችዎ በሙሉ መዘርዘር አለብዎት። በኦንላይን ማመልከቻ ላይ፣ እስከ 16 ቀጣሪዎችን ለመዘርዘር ይችላሉ። ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ ከ16 በላይ ለሚሆኑ ቀጣሪዎች ከሰሩ፣ የክፍያ ጥያቄዎን ማቅረብ የሚችሉት ለክፍያ መጠየቂያ ማዕከል በመደወል ነው።
- **ለሁሉም ቀጣሪዎችዎ የሰሩባቸው ቀናት በሙሉ።** ትክክለኛ ቀናቱን የማያስታውሱ ከሆነ፣ ተቀራራቢ ግምትዎን ይጠቀሙ። ይህን መረጃ አሰሪዎ ስለማያቀርብልን እርስዎ ሪፖርት ማድረግ አለብዎት። እነርሱ ሪፖርት የሚያደርጉልን ደመወዝዎንና የሰሩበትን ሰዓት ብቻ ነው።
- **አብዛኛውን ጊዜ ስራዎትን የሚያገኙት በዩኒየን በኩል ከሆነ፣** የዩኒየንዎን **ስም** እና **የአካባቢ ቁጥር**።
- **ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በጦር ሃይል ውስጥ ከነበሩ፣** የእርስዎ **DD214**፣ ማንኛውም የአባልነት ቅጂ፣ ከ2 እስከ 8።
- **ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የፌዴራል መንግስት ሰራተኛ ከነበሩ፣ Standard Form 8** (SF8) --የስራ አጥነት ኢንሹራንስን በተመለከተ ለፌዴራል ሰራተኞች የተሰጠ ማስታወቂያ፣ እና **Standard Form 50** (SF50) --በሰራተኞች ላይ የሚወሰድ እርምጃ ማስታወቂያ ባያስፈልግም፣ የክፍያ ጥያቄዎ በፍጥነት እንዲከናወን ያግዛል።
- **የዩናየትድ ስቴትስ ዜጋ ካልሆኑ፣** ከ United States Citizenship and Immigration Services (USCIS፣ የዩናይትድ ስቴትስ የዜግነትና ኢሚግሬሽን አገልግሎት) የተሰጠ **የውጭ ዜጋ የምዝባ ቁጥርዎ**።

መረጃዎትን አንዴ ዝግጁ ካደረጉ፣ እዚህ ማመልከት ይችላሉ። (https://secure.esd.wa.gov/home/) ተጨማሪ ድጋፍ ካስፈለገዎ፣ Unemployment Law Project ነጻ የሕግ ድጋፍ ያቀርባል። ለተጨማሪ መረጃ ወደ ድረ ገጻቸው መግባት ይችላሉ ወይም በስልክ ቁጥር 206-441-9178 ይደውሉላቸው። ለሁሉም ቋንቋዎች ነጻ የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል። (http://unemploymentlawproject.org/covid-19/)

# የቤት አገልግሎት

### የወለድ አገድ እና የኪራይ ክፍያ

በአለም አቀፍ ወረርሽኙ ምክንያት የወሩን የወለድ አገድ ወይም የኪራይ ክፍያ ለመክፈል ካልቻሉ፣ አከራይዎን ወይም አበዳሪዎን በአስቸኳይ ያነጋግሩ። በርካታ አበዳሪዎች የቤት ባለቤቶችን የዕዳ መክፈያ ጊዜ እያራዘሙ ነው።

***ነዋሪዎችን ከቤት የማስወጣት እርምጃ በጊዜያዊነት ስለመታገዱ*** - Governor Inslee በመላው ግዛቱ ውስጥ ነዋሪዎችን ከቤት የማስለቀቅ እርምጃዎች እስከ ኤፕሪል 17 በጊዜያዊነት መታገዳቸውን አውጀዋል፤ ይህም ማለት፣ እርስዎ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቤትዎን እንዲለቅቁ አይደረጉም ማለት ነው። በተለይም፣ አከራዮች "የተከራዩን ወይም የሌሎችን ግለሰቦች ጤንነትና ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ" ካልሆነ በስተቀር የ20 ቀናት ማስጠንቀቂያ እንዳይጡ አዋጁ ይከለክላል። የቤት ኪራይዎን ባለመክፈልዎ ምክንያት አከራዮች ክስ ሊያቀርቡብዎም አይችሉም። በመጨረሻም፣ የሕግ አስከባሪው አካል ከቤት የማስለቀቅ ትእዛዞችን ከማስፈጸም ታግዷል። (የሃገረ ገዥው ጽ/ቤት)
የቤትዎን ሁኔታ በተመለከተ እገዛ ካስፈለገዎት፣ ሊያግዙዎ የሚችሉ የተለያዩ ድርጅቶች አሉ።

- **Catholic Community Services** - (206) 323-6336 - (https://ccsww.org/get-help/king-county/)
- **El Centro De La Raza** - (206) 329-0786 - (http://www.elcentrodelaraza.org/get-help/housing-economic-development/)
- **Washington Homeownership Hotline** - (877) 894-4663 -. (https://dfi.wa.gov/homeownership)
- **Saint Vincent de Paul Financial Assistance** - (206) 767-6449 - (https://svdpseattle.org/get-help/online-help-request-form/)
- **World Relief Seattle** - (253) 277-1121 - (https://worldreliefseattle.org/)
- **Men's homeless shelter -** በ Kent፣ Renton፣ እና Federal Way ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ምልመላ የሚካሄደው በ Catholic Community Services SKC Shelter services (253) 854-0077 በኩል ነው(https://ccsww.org/get-help/shelter-homeless-services/)
- **King County Women's Winter shelter** - YWCA Angeline's 2030 3rd Ave Seattle (between Lenora and Virginia). ሴቶች በ Women's Referral Center (የሴቶች ሪፈራል ማዕከል) ውስጥ ዘወትር ከ 6 PM - 9 PM መመዝገብ ይችላሉ። ከ 9 PM በኋላ በስልክ ቁጥር (206) 436-8650 መልእክት ይላኩ ወይም ይደውሉ።
- **Hospitality House** - ላላገቡና ልጅ ለሌላቸው ሴቶች አገልግሎት ይሰጣል at 16003 14th Ave SW, Lake Burien Presbyterian Church. Screenings at (206) 242-1860
- **REACH Center** - ለሴቶችና ሕጻናት ዕለታዊ መጠለያ (ለቤተሰቦች የተወሰነ ማደሪያ መጠለያ) 1055 S Grady Way- P2, (425) 277-7594, ዕለታዊ መጠለያ ብቻ 8 PM - 5 PM ከሰኞ እስከ አርብ። REACH ምግብ፣ ልብስ፣ የልብስ እጥበትና የሻወር አገልግሎት ያቀርባል። (https://www.reachrenton.org)
- **Youth Housing Connection for Homeless Young Adults 18-25** - በቀኑና በሰዓቱ መሰረት በተለያዩ ኤጀንሲዎች በአካል ቀጠሮ መያዝ ይቻላል፣ ለመረጃ በስልክ ቁጥር (206) 328-5796 ይደውሉ።
- ለሰው ልጅ መኖሪያነት በማያመቹ ቦታዎች ለሚኖሩ ቤት አልባ ቤተሰቦች **Family Housing Connection** 2-1-1 ወይም 1-800-621-4636። ቤተሰቦች መኖሪያቸው ጎዳና ላይ ወይም መኪና ውስጥ መሆን አለበት ማለት ነው። በሞቴል ውስጥ መቆየት ወይም ክፍል መጋራት ብቁ አያደርግም።

- **Tent Cities - Seattle** (206) 399-0412 -አገልግሎቱ መኖሩን ደውለው ይጠይቁ። በራስ የሚተዳደሩ የወንዶች፣ የሴቶችና የጥንዶች የቤት ውጭ ካምፖች። የቦታ አድራሻዎች ይቀያየራሉ።

**አሁን ያለውን አከራዬን በተመለከተ ድጋፍ ማግኘት የምችለው የት ነው? →** የተከራዮች ሕብረት (206) 723-0500 (https://tenantsunion.org)

**ከቤቴ እንድለቅቅ እየተደረግኩ ነው - ምን ማድረግ አለብኝ/ለእርዳታ ለማን መደወል አለብኝ → 2-1-1**

**የድንገተኛ ጊዜ/የመሸጋገሪያ ቤት**
YMCA 206-461-4882

**የቤት ኪራይ ድጋፍ**
Hope Line 425-869-6000
Hope link (Eastside) 425-943-7555
Solid Ground Tenant Services 206-694-6767
Community Information 206-461-3200
Housing & Essential Needs Programs 206-328-5755
King County Crisis Clinic 1800-621-4636 or 206-461-3222
Supportive Services for Veteran Families 206-545-2344

Catholic Community Services: 206-323-6336 or Emergency Assistance program 253-850-2523

Seattle ውስጥ የሚገኙ የመረጃ ምንጮችን ዝርዝር. (https://tinyurl.com/uopjdql) እዚህ ማግኘት ይችላሉ
በመላው ግዛት ውስጥ የሚገኙ የመረጃ ምንጮችን ዝርዝር. (https://tinyurl.com/w4anaa5) እዚህ ማግኘት ይችላሉ

# መሰረታዊ አገልግሎቶች

Governor Inslee በ Washington ግዛት ውስጥ ለሚገኙ መሰረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች ባደረጉት ጥሪ፣ በዚህ ድንገተኛ ክስተት ወቅት የአገልግሎት ክፍያ ያልከፈሉ ደንበኞችን መስመር የማቋረጫ ክፍያ እንዲያግዱ፣ ከስራ ውጭ ለሆኑ ደንበኞች ክፍያ በመዘግየቱ ቅጣት እንዳያስከፍሉ ወይም ለደንበኞች የክፍያ ዕቅዶችን እንዲያቀርቡና በዚህ ድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ጫና ለደረሰባቸው ደንበኞች የክፍያ እገዛ ፕሮግራሞችን እንዲያስፋፉ ጠይቀዋል.

**መሰረታዊ አገልግሎቶች**

- **Snohomish Public Utility District** በዚህ ወቅት የደንበኞችን መስመር አያቋርጥም። ለተጨማሪ መረጃ፣ ለደንበኞች አገልግሎት በስልክ ቁጥር 425-783-1000 ይደውሉ ወይም ይህን ድረ ገጻቸውን ይጎብኙ። (https://www.snopud.com/Safety/covid19.ashx?p=3792)
- **Puget Sound Energy** የደንበኞችን መስመር አያቋርጥም፣ የዘገየ ክፍያ ቅጣት አያስከፍልም፣ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ደንበኞች የገንዘብ ድጋፍ መስጫ ፖርታልአዘጋጅቷል። (https://www.pse.com/pages/bill-and-weatherization-assistance)
- **Seattle Public Utilities (SPU) and Seattle City Light (SCL)** የክፍያ ጊዜን የማራዘም ዕቅድ አዘጋጅተዋል። የ COVID-19 ቀውስ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ፣ መሰረታዊ የአገልግሎት ክፍያዎትን ባይከፍሉም እንኳን በመላው Seattle ውስጥ አገልግሎት አይቋረጥም። የመኖሪያ ቤት ደንበኞች ወደ 206-684-3000 በመደወል ወይም ለ seattle.gov/utilities/about-us/email-question ኢሜይል በመላክ ከ SPU ወይም SCL ጋር የክፍያ ማራዘሚያ ዕቅድ ማውጣት ይችላሉ።
- **Tacoma Public Utilities** - የከተማው ምክር ቤት የከተማው የውሃ፣ የፍሳሽ፣ የማዕበል ውሃና የደረቅ ቆሻሻ መ/ቤት ክፍያ ያልከፈሉ ነዋሪዎችን አገልግሎት የማቋረጥ እርምጃን ለሌላ ጊዜ እንዲያራዝም ትእዛዝ ሰጥቷል። ምክር ቤቱ በተጨማሪም Tacoma Public Utilities የድንገተኛ ጊዜ ድጋፍ ፕሮግራም እንዲጀምር ፈቃድ የሰጠ ሲሆን ይህም የተደረገው ተጨማሪ ቁጥር ያላቸው ቤተሰቦች ለድጋፉ ብቁ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው። ብቁ መሆንዎትን ለማወቅና ለማመልከት ይህን ገጽ ይጎብኙ። (https://www.mytpu.org/emergencyassistance/)

**ኢንተርኔት (ብሮባንድ እና Wi-Fi)**

- **Comcast** - Comcast ለ Internet Essentials ደንበኞቹ የሁለት ወር ኢንተርኔት በነጻ ይሰጣል። ኬብል ሞደም ከ Wi-Fi ራውተር ጋር ያለው ራሱን የሚጭን ኪት ይደርስዎታል። ተጨማሪ መረጃዎችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ።
- **Xfinity Hotspots** - የ Xfinity Wi-Fi ሆትስፖቶች ለ60 ቀናት ያህል ለማንኛውም ሰው ነጻ የሚደረጉ ሲሆን፣ ይህም የ Xfinity ደንበኞች ያልሆኑትንም ይጨምራል። ሁሉም ደንበኞች ያልተገደበ ዳታ በነጻ ያገኛሉ፤ ደንበኛው ሁኔታውን ለ Comcast እስካሳወቀ ድረስ ደግሞ ክፍያ የዘገየበት ቅጣት ወይም የአገልግሎት ማቋረጥ አይኖርም።
- **CenturyLink** - CenturyLink ለ60 ቀናት የዘገየ ክፍያ ቅጣትን አያስከፍልም፣ ለደንበኞቹ ያልተገደበ ዳታ ያቀርባል፣ እንደዚሁም ክፍያ ባለመከፈሉ ምክንያት አገልግሎት አያቋርጥም።
- **AT&T** - AT&T ለ60 ቀናት ነጻ የ WIFI ሆትስፖት ያቀርባል፣ የዘገየ ክፍያ ቅጣት ይሰርዛል፣ እንደዚሁም ክፍያ ባለመከፈሉ ምክንያት አገልግሎት አያቋርጥም። እንደ Comcast ሁሉ፣ AT&T ለሕዝቡ ነጻ የ Wi-Fi ሆትስፖቶችን ያቀርባል። በተጨማሪም፣ የመኖሪያ ቤት ኢንተርኔት ዋየርላይን ደንበኞቹና የገመድ አልባ ኢንተርኔት ደንበኞቹ ያልተገደበ ዳታ ያገኛሉ።
- **Verizon** - Verizon ለ60 ቀናት ነጻ የ Wi-Fi ሆትስፖት ያቀርባል፣ የዘገየ ክፍያ ቅጣት ይሰርዛል፣ እንደዚሁም ክፍያ ባለመከፈሉ ምክንያት አገልግሎት አያቋርጥም።
- **T-Mobile** - T-Mobile የዳታ ዕቅድ ላላቸው ወቅታዊ ደንበኞቹ በሙሉ ለቀጣዮቹ 60 ቀናት ያልተገደበ ዳታ ያቀርባል። ለሞባይል ሆትስፖት ተጠቃሚዎች ተጨማሪ ዳታ ያቀርባሉ።

# የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ

**Temporary Assistance for Needy Families (TANF)** ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ የጥሬ ገንዘብና የሕክምና ድጋፍ ይሰጣል። ስደተኞችና ፍልሰተኞች የፕሮግራሙን መስፈርት ካሟሉ ለ TANF ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ሃገረ ገዥው የ Family Emergency Assistance Program የብቁነት መስፈርቶች ያሰፉ ሲሆን፣ ይህም ልጅ የሌላቸውን ቤተሰቦች ለማካተት እንዲቻል ነው። (DSHS)

ለ TANF ብቁ ለመሆን፣ ቤተሰብዎ ያለው ሐብት $6,000 ወይም ከዚያ በታች መሆን አለበት። ሐብቶች የሚባሉት የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡

- የተንቀሳቃሽና የቁጠባ ሒሳቦች
- አክሲዮን፣ ቦንድ ወይም የጋራ ገንዘቦች
- ከ $10,000 በላይ ያለው የተሽከርካሪ ድርሻ

ብቁ መሆንዎትን ለማወቅ፣ በቅድሚያ የቅድመ ማጣሪያ የዳሰሳ ጥናቱን ይሙሉ። ከዚያም፣ ለማመልከት፣ ቅጹን ይሙሉ። ቅጹን ለመሙላት ወደ 60 ደቂቃ የሚፈጅ ሲሆን፣ ማጣሪያው ደግሞ ከ 30-45 ቀናት ይፈጃል። በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ፕሮግራሞች ማመልከት ይችላሉ።

የቅድመ ማጣሪያ ዳሰሳ ጥናት፡- https://tinyurl.com/v2tlx83
ማመልከቻ፡- https://tinyurl.com/tuhfsgn

ማመልከቻውን በሌላ ቋንቋ ለመሙላት ከፈለጉ፣ በመረጡት ቋንቋ ቅጹን ማውረድ ይችላሉ። (https://www.dshs.wa.gov/office-of-the-secretary/forms?field_number
_value=14-001&title=)

**የማህበረሰብ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች**

- **National Domestic Workers Alliance Fund** - የቤት ውስጥ ሰራተኛ ከሆኑ (ለምሳሌ፡ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ፣ ሞግዚት እና/ወይም የጽዳት ሰራተኛ)፣ ከዚህ ፈንድ የ $400 የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። እዚህ ማመልከት ይችላሉ: https://membership.domesticworkers.org/coronavirus-care-fund/

- **One Fair Way Emergency Fund** - በአገልግሎት ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ፣ ከዚህ ፈንድ የጥሬ ገንዘብ ስጦታ ለማግኘት ይችላሉ. You can apply here: https://ofwemergencyfund.org/help

- **Seattle Hospitality Emergency Fund** - በአለም አቀፉ ወረርሽኝ ምክንያት የስራ ሰዓታቸው የተቀነሰና ሌላ ማካካሻ የማያገኙ የመስተንግዶ ዘርፍ ሰራተኞች የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ። እዚህ ማመልከት ይችላሉ፡ https://www.surveymonkey.com/r/CHD7ZRY

**The Plate Fund**- በ King County ውስጥ ለሚኖሩና በ COVID-19 ቀውስ ምክንያት የስራ ሰዓታቸው የተቀነሰ ወይም ከስራ የተሰናበቱ የምግብ አገልግሎት ወይም የሬስቶራንት ሰራተኞች የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ፤ እነርሱም፣ ሰሃን አጣቢዎች፣ ምግብ አብሳዮች፣ አስተናጋጆች፣ ባሬስታዎች፣ የምግብ ጫኝ መኪና ሰራተኞችና የካፌ አስተናጋጆች። ቀደም ሲል ከመንግስት ድጋፍ እያገኙ ያሉ ሰዎች ማመልከት አይችሉም፣ ምክንያቱም ችግረኛ ቤተሰቦች እነዚህን የድንገተኛ ጊዜ ፈንድ ለመጠቀም እንዲችሉ ነው

## የምግብ ድጋፍ

**COVID-19 Mutual Aid Solidarity Network** - ምግብ ወይም ሌሎች አቅርቦቶችን ከፈለጉና መኖሪያዎትም በ Seattle አካባቢ ከሆነ፣ ይህን ቅጽ ይሙሉ የቤትዎ በር ድረስ እንዲመጡልዎ የሚፈልጓቸውን ዕቃዎችም ይዘርዝሩ። ከመደብር ሸመታዎ ውስጥ እስከ $50 ድረስ ይሸፍናሉ . (https://tinyurl.com/whspv2n)

**COVID-19 South King County and Eastside Mutual Aid** - ምግብ ወይም ሌሎች አቅርቦቶችን ከፈለጉና መኖሪያዎትም በ South King County ወይም Eastside ውስጥ ከሆነ፣ ይህን ቅጽ ይሙሉ የቤትዎ በር ድረስ እንዲመጡልዎ የሚፈልጓቸውን ዕቃዎችም ይዘርዝሩ። ከፈለጉ፣ ከመደብር ለሚሸምቷቸው ዕቃዎች የገንዘብ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። (https://tinyurl.com/ud8955o)

**ለመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች የሚሰጥ የምግብ ድጋፍ**
ት/ቤቶች ቢዘጉም፣ በመላው King County ውስጥ የሚገኙ በርካታ የት/ቤት ዲስትሪክቶች ሳምንቱን በሙሉ ምሳ ያከፋፍላሉ። ተማሪዎች ያላቸው ቤተሰቦች መሳተፍ ይችላሉ። እባክዎ የምግብ ማደያ ቦታዎችን ለማወቅ የአካባቢዎን ት/ቤት ዲስትሪክት ድረ ገጽ ይጎብኙ።

**FEEST Seattle በ FEEST ት/ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ላላቸው ቤተሰቦች በነጻ የሚሰጥ አስቤዛ**
በ Chief Sealth፣ Evergreen፣ Rainier Beach እና Tyee High Schools ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ያላቸው ቤተሰቦች ነጻ አስቤዛ ወደቤታቸው እንዲመጣላቸው መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎ ማድረግ ያለብዎት ኦንላይን ቅጽ በመሙላት የሚሸምቱትን ዕቃ መዘርዘር፣ የመገኛ አድራሻዎን መጻፍና ዕቃው መቼ እንዲደርስልዎ እንዲፈልጉ መግለጽ ብቻ ነው። አስቤዛ እንዲዝልዎት ለመጠየቅ ይህን ማስፈንጠሪያ ይጠቀሙ፡- https://www.feestseattle.org/grocery-delivery-for-feest-families/

**WA-BLOC ለ Rainier Beach ማህበረሰብ የሚደረግ የምግብ ድጋፍ**
WA-BLOC ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ለሚቆዩበት ወቅት በ Rainier Beach Community ለሚኖሩ ተማሪዎች ዘወትር ማክሰኞና ሐሙስ ከ 1:00 PM እስከ 3:00 PM በ Rainier Beach Community Center ፕላዛ ውስጥ ነጻ ትኩስ ምሳ ያቀርባል።ተጨማሪ መረጃዎችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡የ WA-BLOC Facebook ገጽ። (https://www.facebook.com/pg/wabloc/posts/?ref=page_internal)

**Northwest Harvest SODO Community Market**
Northwest Harvest SODO Community Market አስቀድመው የታሸጉ ምርቶችን፣ የበሰሉ ምግቦችንና መደርደሪያ ላይ የሚቀመጡ ምግቦችን ከበሩ እንድትወስዱ አቅርቧል። ወደ ድርጅቱ ውስጥ መግባት አያስፈልግም። በሁሉም ዕድሜ ላይ ለሚገኙ ሰዎች ክፍት ነው። SODO Community Market የሚገኝበት አድራሻ በ Seattle የ SODO አካባቢ 1915 4th Ave S, ከ 4th Ave S & S Holgate St. ማዕዘን አጠገብ ነው። ተጨማሪ የአድራሻና የትራንስፖርት መረጃን እዚህ ማግኘት ይቻላል: https://www.northwestharvest.org/sodo-community-market

**Meals on Wheels**
Meals on Wheels ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ ለሆናቸውና ከቤታቸው መውጣት ላልቻሉ ግለሰቦች ነጻ ምግብ እቤታቸው ድረስ ያቀርባል። ዕድሜዎ ከ60 ዓመት በታች ከሆነ፣ ምግብ እንዲቀርብልዎት ለአንድ ምግብ $7 መክፈል ይችላሉ። ኦንላይን እዚህ ማመልከት ይችላሉ: https://www.tfaforms.com/4734393

**Food Lifeline**
በአቅራቢያዎ ያለውን የምግብ ባንክ ለማግኘት፣ የዚፕ ኮድዎን እዚህ ያስገቡ: https://foodlifeline.org/need-food/

## የሕጻናት መዋያ

ት/ቤቶች ተዘግተው እያለ ስራ መስራት ካስፈለገዎ፣ WA Department of Social and Health Services (የዋሽንግተን የማህበራዊና ጤና አገልግሎቶች መምሪያ) የሚያቀርባቸውና የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች አሉ።

**Child Care Aware** ቤተሰቦች ከቤታቸው እና/ወይም ከስራ ቦታቸው አጠገብ የልጆች እንክብካቤ አገልግሎትን ለመደገፍ የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው። አማራጭ የልጆች እንክብካቤን እንዲያገኙ ከሚያግዝዎት ቡድን ጋር ለመገናኘት ድረ ገጹን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 800-446-1114 ይደውሉ።
(https://childcareawarewa.secure.force.com/providerupdate/CCAWAOnlineLookUp)

የግዛቱ **የቤተሰቦች፣ የጓደኞችና የጎረቤት ፕሮግራም** አያቶችን፣ አክስቶችንና አጎቶችን፣ አረጋውያን፣ ታላቅ እህት ወይም ወንድም፣ ጓደኞችን፣ ጎረቤቶችንና የልጅ እንክብካቤ በማድረግ ቤተሰቦችን የሚያግዙ ሌሎች ሰዎችን ያካትታል። አንዳንድ ቤተሰቦች ለተንከባካቢያቸው ክፍያ ለመፈጸም ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ ድረ ገጹን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 866-482-4325 ይደውሉ።
(https://www.dcyf.wa.gov/services/earlylearning-childcare/ffn)

**ለተማሪዎች በነጻ የሚሰጥ የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት** - ተማሪዎችን ለማገዝ፣ በትስስር ውስጥ ለመቆየትና በት/ቤት ለመቆየት እንዲችሉ፣ Altice ለሁሉም K-12 እና የኮሌጅ ተማሪዎች ለ60 ቀናት የሚቆይ ነጻ የብሮድባንድ ኢንተርኔት አቅርቧል። እዚህ ማመልከት ይችላሉ፡- https://www.alticeusa.com/news/articles/feature/corporate/altice-usa-brings-free-broadband-k-12-and-college-students-during-coronavirus-pandemic

**የ Seattle ከተማ ወሳኝ ሰራተኞች አጣዳፊ የልጆች እንክብካቤ ቅጽን እዚህ ማግኘት ይቻላል።**
**መኖሪያዎት ወይም የስራ ቦታዎት በ King County ውስጥ የሆነ ወሳኝ ሰራተኛ ከሆኑና ነጻ የአጣዳፊ የልጆች እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎ ለ Child Care Aware of Washington Family Center በስልክ ቁጥር 1-800-446-1114** ይደውሉና ለ Family Center ሰራተኛ መረጃ ይስጡ። መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ፣ የመረጃዎች ስፔሻሊስት ከእርስዎ ጋር በመስራት የቤተሰብዎን ፍላጎት የሚያሟላ ብቁ የሕጻናት እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ያገናኝዎታል። የስራ ቅጥር እና/ወይም የአድራሻ ትክክለኛነት ማረጋገጫ ያስፈልጋል።

**እባክዎ ያስተውሉ፡-** ሒደቱን ለማፋጠን፣ አስፈላጊ የማረጋገጫ ሰነዶችን ወደ **subsidy@childcare.org** ይላኩ።

**የአሰሪ ማረጋገጫ፡-** የሰራተኛውንና የአሰሪውን ስም፣ የስራ ቦታ የሚገኝበትን አካላዊ አድራሻ ማካተት አለበት። ከሚከተሉት መካከል የአንዱን ፎቶ መላክ በቂ ነው፡-

- የስራ መታወቂያ ባጅ፤
- ከስራ አድራሻ የተላከና በፊርማ ቦታ ላይ ስምና የመገኛ አድራሻ ያለበት ኢሜይል፤
- የቢዝነስ ካርድ **ወይም** የክፍያ ማስረጃ **ወይም** የስራ መርሃ ግብር።

ሰነዱ ከተሰጠ ከ3 ወር ያለፈው መሆን የለበትም፣ የሰራተኛውን ስም ማካተት አለበት፣ ኤንቨሎፕ ወይም የግል መልእክት ልውውጥ መሆን የለበትም። **የቤት አልባነት ችግር ካጋጠመዎት ወይም የመኖሪያ አድራሻዎን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካልቻሉ፣ እባክዎ ያሳውቁንና አማራጭ የማረጋገጫ ዘዴን እናቀርባለን።**

- ከዚህ ዝርዝር ውስጥ **አንድ** ያቅርቡ፡-
  - የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ (ጋዝ፣ ውሃ/ቆሻሻ፣ መብራት/ኤሌክትሪክ፣ ኬብል፣ ባለገመድ ስልክ)
  - የቤት/የአከራይ ኢንሹራንስ
  - የወለድ አገድ ክፍያ ወይም ከተለያዩ ምንጮች ከዚህ ዝርዝር ውስጥ **ሁለት**፡- ሌሎች የክፍያ ደረሰኞች፣ የመንጃ ፈቃድ፣ የጥቅማ ጥቅም ሰነዶች ((DSHS, SSI፣ የክፍያ ደረሰኝ፣ ወዘተ)፣ የኢንሹራንስ ሰነድ (የጤና፣ መኪና፣ ወዘተ)፣ የፋይናንስ ሰነድ (የባንክ መግለጫ፣ የጡረታ ክፍያ፣ የክሬዲት ካርድ መግለጫ) ወይም የሊዝ ወይም የቤቶች ኤጀንሲ ደብዳቤ

# ለሰነድ አልባ ፍልሰተኞች የሚያገለግሉ የመረጃ ምንጮች

ሰነድ አልባ ከሆኑ፣ ለፌዴራልና ለግዛት ድጋፍ ብቁ ላይሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በዚህ ጊዜ ሊረዱዎት የሚችሉ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት አሉ።

**የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች**

የፋይናንስ ችግር ካጋጠመዎት፣ ሊያመለክቱባቸው የሚችሉ የተለያዩ ፈንዶች አሉ።

- **Betancourt Macias Family Emergency Fund** - ማንኛውም ሰነድ አልባ ግለሰብ ለፈንዶች እዚህ ማመልከት ይችላል: https://www.undocuscholars.com
- **National Domestic Workers Alliance** - የቤት ውስጥ ሰራተኛ ከሆኑ (ለምሳሌ፡ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ፣ ሞግዚት እና/ወይም የጽዳት ሰራተኛ)፣ ከዚህ ፈንድ የ $400 የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። እዚህ ማመልከት ይችላሉ፡- https://membership.domesticworkers.org/coronavirus-care-fund/
- **One Fair Way Emergency Fund** - በአገልግሎት ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ፣ ከዚህ ፈንድ የጥሬ ገንዘብ ስጦታ ለማግኘት ይችላሉ። እዚህ ማመልከት ይችላሉ፡- https://ofwemergencyfund.org/help
- **DACA የእድሳት ስኮላርሺፕስ** - El Centro De La Raza ለ DACA እድሳት ክፍያ ለመፈጸም የገንዘብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች ስኮላርሺፕ ይሰጣል። ለ Department of Homeland Security (የሃገር ውስጥ ደህንነት ሚኒስቴር) ተከፋይ የሆነ ቼክ ይልካሉ። ቅጹን እዚህ ያቅርቡ: http://www.elcentrodelaraza.org/get-help/daca/?fbclid=IwAR3rhuFR-XBXrEQ_DsuVPIZ8C-EUmYGZb4RFcBv7tiBr33KJbMMi4ePvORQ
- **COVID-19 Relief Fund for WA Undocumented Folks** - ማመልከቻዎች ኤፕሪል 8 የሚጀምሩ ሲሆን፣ ለአንድ ግለሰብ ከ $500 - $1,500 የሚደርስ እርዳታ እንደሚያከፋፍሉ ይገምታሉ። ይህን ቅጽ በመሙላት የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይግቡ: https://tinyurl.com/vh2c8k4

# ለሰነድ አልባ ፍልሰተኞች የሚያገለግሉ የመረጃ ምንጮች የቀጠለ

### የጤና እንክብካቤ ማግኘት

ከሁሉ በፊት — እንክከካቤ ካስፈለገዎት፣ ወደ ዶክተር ይሂዱ። ለራስዎ ደህንነትና በዙሪያዎት ላሉ ሰዎች ደህንነት ሲባል፣ የሕመም ምልክቶች ካሉብዎ የጤና እንክብካቤ ማግኘትዎ አስፈላጊ ነው። ማስታወስ የሚገቡን አንዳንድ ወሳኝ መረጃዎች እነዚህ ናቸው፡-

- ዋስትና ከሌለዎት፣ የጤና ምርመራ የሚደረግልዎ በነጻ ሲሆን ወጪውን የሚሸፍነው National Disaster Medical System (ብሔራዊ የአደጋ ሕክምና ስርዓት) ነው።
- የጉብኝትዎን ሚስጥራዊነት የሚጠብቁ ጥብቅ የሆኑ ሕጎች አሉ። የኢሚግሬሽን ሕግ አስፈጻሚ አካላት በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ካልሆነ በስተቀር እንደ ሆስፒታል፣ የጤና ክሊኒክና አጣዳፊ የጤና እንክብካቤ ተቋማት ባሉ የጤና እንክብካቤ ተቋማት ውስጥ ሰዎችን የማሰር ተግባር እንዳያከናውኑ ተከልክለዋል።
- ወደ ዶክተር ለመቅረብ የጤና ኢንሹራንስ አያስፈልግዎትም። የማህበረሰብ ጤና ማዕከላት የሰዎች የኢሚግሬሽን ሁኔታ ምንም ቢሆን የጤና እንክብካቤ በነጻና በዝቅተኛ ክፍያ ይሰጣሉ።
  - በአቅራቢያዎ ያሉ የጤና ማዕከላትን ያግኙ: https://findahealthcenter.hrsa.gov/
  - ነጻ እና የበጎ አድራጎት ሰጪ ክሊኒኮችን ያግኙ፡- http://www.nafcclinics.org/find-clinic
- የጤና እንክብካቤ ሲያገኙ ስለሚኖሩዎት መብቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን የእውነታ ቅጽ ያንብቡ፡- https://protectingimmigrantfamilies.org/wp-content/uploads/2020/02/You-Have-Rights-Protect-Your-Health-Updated-February-2020-ENGLISH.pdf

**የቤት አገልግሎት** — ከላይ የተዘረዘሩት የቤት ድጋፍ ፕሮግራሞች በሙሉ ለሰነድ አልባ ፍልሰተኞች ይቀርባሉ። ከላይ "የቤት አገልግሎት" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

**ምግብና አቅርቦቶች** — ከላይ የተዘረዘሩት የምግብ ድጋፍ ፕሮግራሞች በሙሉ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ምንም ቢሆን ለሁሉም ሰው የሚቀርቡ ናቸው። ከላይ "የምግብ ድጋፍ" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

ይህን ስፕሬድሺት በማየት ለሰነድ አልባ ፍልሰተኞች የሚሆኑ የመረጃ ዝርዝሮችን በተከታታይ ማየት ይችላሉ፡- https://tinyurl.com/wrmeqhk

# የአነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ብድር እና የአደጋ ጊዜ ድጋፍ

Payroll Protection Program

የንግድ ድርጅቶች በኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ቀውስ ወቅት የሰራተኛ ሐይላቸውን ጠብቀው እንዲያቆዩ የሚያግዝ የ SBA ብድር።

Coronavirus (COVID-19) SBA Disaster Assistance

የ U.S. Small Business Administration (የዩ.ኤስ አነስተኛ ንግድ አስተዳደር) ለተወሰኑ ግዛቶችና ክልሎች ዝቅተኛ ወለድ ያለው የፌዴራል የአደጋ ጊዜ ብድር ያቀረበ ሲሆን፣ ብድሩም በኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለደረሰባቸው አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች የመንቀሳቀሻ ካፒታል የሚውል ነው።

Coronavirus (COVID-19) SBA Relief Options

እርዳታ ለሚፈልጉ አካላት በርካታ የገንዘብ ድጋፍ አማራጮች አሉ

The CARES (Coronavirus Aid, Relief and Economic Security) Act Frequent Questions

Association of Washington Businesses (AWB፣ የዋሽንግተን ቢዝነሶች ማህበር) ከ COVID-19 ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶችን የያዘ ገጽ አለው።

Coronavirus (COVID-19) SBA Guidance and Resources

የኮሮና ቫይረስ የገንዘብ ድጋፍ አማራጮች እና የንግድ ድርጅቶችና የአሰሪዎች መመሪያዎች

Other SBA Funding Programs

ከ SBA የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ጋር ያገናኛል

How SBA Loan Programs Work

SBA ከአበዳሪዎች ጋር አብሮ በመስራት ለአነስተኛ ድርጅቶች ብድሮችን ያቀርባል። ኤጀንሲው ለአነስተኛ የንግድ ድርጅት ባለቤቶች በቀጥታ ገንዘብ አያበድርም። ከዚህ ይልቅ፣ አጋር አበዳሪዎቹ፣ የማህበረሰብ ልማት ድርጅቶችና ማይክሮ አበዳሪ ተቋማት ለሚሰጧቸው ብድሮች መመሪያዎችን ያስቀምጣል። SBA የአበዳሪዎችን ስጋት በመቀነስ ካፒታል በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ይህ ደግሞ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ብድር በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

Washington State's Central COVID-19 Webpage

ይህ የ Washington ግዛት ይፋዊ የ COVID-19 ድረ ገጽ ሲሆን፣ የሚያስተዳድረውም የግዛቱ Joint Information Center (JIC፣ ጥምር የመረጃ ማዕከል) ነው። The JIC በ Camp Murray የሚመራው የ Washington State Emergency Operations Center አንድ አካል ነው። ድረ ገጹ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን የያዘ ነው፡ ለንግድ ድርጅቶችና ሰራተኞች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ፣ ለንግድ ድርጅቶች የኢንሹራንስ መረጃ፣ የአነስተኛ ንግድ ድርጅቶች ብድሮችና ለአነስተኛ የንግድ ድርጅቶችና ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶች የመረጃ ምንጮች

Startup Washington የተለያዩ የግዛትና የፌዴራል መሳሪያዎችና የመረጃ ምንጮችን ያካተተ ነው።

## KING COUNTY በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የመረጃ ምንጮች

| KING COUNTY<br><br>በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የመረጃ ምንጮች | የ WASHINGTON ግዛት<br><br>እና በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የመረጃ ምንጮች |
|---|---|
| ○ Amharic<br>○ Arabic<br>○ Chinese<br>○ Dari<br>○ Filipino – Tagalog<br>○ French<br>○ Hindi<br>○ Hmong<br>○ Japanese<br>○ Khmer – Cambodian<br>○ Korean<br>○ Lao<br>○ Marshallese<br>○ Oromo<br>○ Pashto<br>○ Persian (Farsi)<br>○ Somali<br>○ Spanish<br>○ Thai<br>○ Tigrinya<br>○ Ukrainian<br>○ Vietnamese | ○ Washington State COVID Educational Materials 26+<br><br>○ Center for Disease Control (CDC) Resources in Languages other than English<br><br>○ American Sign Language COVID-19 resources<br><br>○ Washington State COVID-19 Video Series<br><br>○ Center for Disease Control (CDC) ASL COVID-19 Video Series<br><br>○ Harvard COVID-19 Fact Sheets in 30 languages |